# በአሉ ግርማ ፋውንዴሽን ከኢትዮጵያ ሴት ደራስያን ማህበር ጋር በመተባበር ለወጣትና አዳዲስ ደራሲያን በግጥምና በአጭር ልቦለድ አጻጻፍ ያዘጋጀው ዐውደ ጥናት

## አጭር ዘገባ

በ

ዘሪሁን አስፋው

አዲስ አበባ፣ የካቲት 6፣2002 ዓ.ም

## 1. መግቢያ

በዐውደጥናቱ የተሳተፉት ደራስያን፣ የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎችና በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የስነጽሁፍና ፎክሎር ድህረምረቃ ተማሪዎች ናቸው። በዐውደጥናቱ ጥናታዊ ጽሁፎቻቸውን ያቀረቡት ሶስት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል መምህራን ናቸው። ዐውደጥናቱ የተካሄደው በሰሜን ሆቴል ሲሆን ከጧቱ በ2:30 ተጀምሮ ከቀኑ 12:00 ተጠናቋል።

በዐውደ ጥናቱ ሶስቱ ባለሙያዎች ጥናታቸውን ካቀረቡ በኋላ ተሳታፊዎች በጥያቄና መልስ ክፍለጊዜ ሀሳባቸውን እንዲገልጹና ውይይት እንዲካሄድ ተደርጓል። ተሳታፊዎቹ ከሰነዘሩዋቸው አስተያየቶችና ምላሾች ዐውደ ጥናቱ በተሳካ ሁኔታ ተጠናቋል ማለት ይቻላል።

## 2. የዐውደ ጥናቱ አጀማመር

ዐውደ ጥናቱ የተጀመረው በአስተባባሪው በዘሪሁን አስፋው የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር ነው። ዘሪሁን በንግግሩ በኢትዮጵያ ስነጽሁፍ ታሪክ በአቢይነት ከሚጠቀሱት ደራሲዎች መካከል በአሉ ግርማ አንዱ መሆኑን፣ በኢትዮጵያ የረጅም ልቦለድ ስነጽሁፍ እንቅስቃሴ የበዓሉ ግርማ ስም ሳይጠቀስ የማይታለፍ መሆኑን፣ በተለይ ደግሞ የ1960ዎቹንና የ1970ዎቹን የረጅም ልቦለድ ዘመን በመክፈት ረገድ ከሚጠቀሱት ሁለት ደራሲዎች መካከል አንዱ በዓሉ ግርማ መሆኑን አውስቷል።

በተጨማሪ በአሉ ግርማ በታሪክ አፈጣጠር፣ በገጸባህሪያት አሳሳልና በቋንቋ አጠቃቀም ከፍ ያለ ዋጋ የተሰጣቸውን ልቦለዶች በማበርከቱ ሁልጊዜ ሲታወስ የሚኖር ደራሲ መሆኑን ገልጿል። በዓሉ ግርማ ከ1962 እስከ 1975 ድረስ ስድስት የማይረሱ፣ ለኢትዮጵያ ስነጽሁፍ ዕድገት ጉልህ ድርሻ ያበረከቱ ልቦለዶችን ያሳተመ ደራሲ መሆኑን በመግለጽ በነዚህ ስራዎቹ ላይ ከ80 በላይ የምርምር ስራዎች የቀረቡ መሆናቸውን ጠቅሷል። በመጨረሻም የዛሬ 2ቾ ዓመት ያጣናው ደራሲ በአሉ ግርማ በአካል ባይኖርም ስራዎቹ ህያው ሆኖ እንዲኖር ያደረጉት መሆናቸውንና ዐውደ ጥናቱም የተዘጋጀው ለዚህ አቢይ ደራሲ መታሰቢያ መሆኑን በማውሳት የዐውደ ጥናቱን አላማ ለተሳታፊዎቹ አስረድቷል።

የኢትዮጵያ ሴት ደራሲያን ማህበር ፕሬዚዳንት የምወድሽ በቀለ የማህበሩን መልዕክት አስተላልፋለች። በንግግሯም ደራሲ በአሉ ግርማ ለኢትዮጵያ ስነጽሁፍ ያበረከተውን ጉልህ ድርሻና የከፈለውን መስዋዕትነት አውስታለች። የኢትዮጵያ ሴት ደራሲያን ማህበርም ከበአሉ ግርማ ፋውንዴሽን ጋር በሚቻለው አቅም ለመስራት ፈቃደኛ መሆኑን ጠቅሳለች።

የበአሉ ግርማን ፋውንዴሽን በመወከል መስከረም በአሉ ባደረገችው ንግግር ፋውንዴሽኑ የተቋቋመበትን አላማ በመግለጽ ፋውንዴሽኑ ለወደፊቱ ሊሰራ ያሰባቸውን ተግባራት ጠቅሳለች። ፋውንዴሽኑ ሊጠናከር የሚችለውም ዛሬ በተገኙት የዐውደ ጥናቱ ተሳታፊ ደራሲዎችና ባለሙያዎች እንዲሁም በሌሎች መሰል የኪነጥበብ ሰዎች ድጋፍ መሆኑን ገልጻለች። በአሉ ግርማ ፋውንዴሽን ከደራስያን፣ ከመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች እንዲሁም ከስነጽኁፍ ምሁራን ጋር አብሮ ለመስራት ፈቃደኛ መሆኑን ገልጻ ተሳታፊዎች በፋውንዴሽኑ አድራሻ አስተያየታቸውንና ሀሳባቸውን መላክ የሚችሉ መሆናቸውን አሳውቃለች። መስከረም የዛሬው ዐውደ ጥናት የመጀመሪያና የሙከራ መሆኑን ተቅሳ ፋውንዴሽኑ ለወደፊት ከዚህ የተሻሉና ሰፋ ያሉ መርሀግብሮችን ለማዘጋጀት ጥረት እንደሚያደርግ ለተሳታፊዎቹ ገልጻለች። በመጨረሻም የዛሬውን ዐውደ ጥናት ለማዘጋጀት የተለያየ አስተዋጽኦ ያደረጉትን በማመስገን ተሳታፊዎቹ የቀኑ ውሏቸው ፍሬያማ እንዲሆን ተመኝታለች።

## 3. በዐውደ ጥናቱ የቀረቡ ትምህርቶች

በዚህ ዐውደ ጥናት በጥናት ላይ ተመስርተው የቀረቡት ትምህርቶች አራት ናቸው ቀጥሎ ስለእያንዳንዳቸው አጠር ያለ አጠቃሎ ተሰጥቷል።

በመጀመሪያ የቀረበው ርእሰ ጉዳይ ሥነጽሁፍንና ጋዜጠኝነትን የተመለከተ ሲሆን አቅራቢዋ አጋረደች ጀማነህ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል መምህር ስትሆን በአሁኑ ጊዜ በኖርዌ የፒኤችዲ ተማሪ ናት። አጋረደች ያቀረበችው ትምህርት በጥቅሉ የሚከተለውን ይመስላል።

የጽሁፏ ዓላማ ስነጽሁፋዊ ስልቶች ለጋዜጣዊ አጻጻፍ ያላቸው አስተዋጽኦና እነዚህንም ስልቶች እስከምንደረጃ ድረስ መጠቀም እንደሚቻል ማስተማር ነው። ትኩረት የተደረገው ከስርጭት መገናኛ ብዙኃን ይልቅ በህትመት መገናኛ ብዙኃን ማለትም በጋዜጣ ላይ ነው። ለዚህም ሶስት መሰረታዊ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ። የመጀመሪያው በዓሉ ግርማ ራሱ በህትመት መገናኛ ብዙኃን ላይ የነበረው ተሳትፎ የጎላ በመሆኑ፣ ሁለተኛው የጽሁፉ አቅራቢ የሥራ ዓለም ተሞክሮ በጋዜጣ ላይ መሆኑ፣ ሶስተኛው ደግሞ የህትመት መገናኛ ብዙኃን እንደሬዲዮና ቴሌቪዥን አጋዥ የምስልና የድምጽ ግብአቶች ስለሌሉት ጸሀፊዎች ሁሉንም እውነት እንደሚታይ፣ እንደሚሰማና እንደሚሸተት አድርገው የመጻፍ ችሎታ ሊኖራቸው የተገባ በመሆኑ ነው።

ጋዜጣዊ አጻጻፍ እውነተኛ መረጃን መሰረት በማድረግ ለተደራስያን ማቅረብ ነው። እንደልበለድና እንደግላዊ ድርሰቶች ምናባዊ አቀራረብን አይፈቅድም። በጋዜጠኝነት ታሪክ ውስጥ እውነተኛ ድርጊቶችን በማስመሰል የቀረቡ፣ የሙያውን ስነምግባር የጣሱ አጋጣሚዎች መፈጠራቸውም በውይይት ላይ ተጠቅሷል። ይሁን እንጂ ስነጽሁፋዊ ጋዜጠኝነት የሙያውን ስነምግባር ሳይጥሱ እውነተኛን ክስተትና ገጠመኝ፣ አዝናኝነት ባለው መልኩ ማቅረብ የዘመኑን አንባቢ ለመማረክ ይረዳል የሚል እሳቤ ያላቸው ወገኖች የሚከተሉት መርህ ነው። እዚህ ላይ የሚነሳ አብይ ነጥብ የመርህ ግጭት ቢፈጠርስ የሚል ነው። ይኸውም ስነጽሁፋዊ ስልቶችን ስራ ላይ ባዋልን መጠን የጋዜጠኝነት መርህ የሆነው ትክክለኛነት አይጣስም ወይ የሚል ነው። ይህን ችግር ለማስወገድ እውነታና መረጃዎች በጊዜና በቦታ የተከናወኑ መሆናቸውን ማረጋገጥ በሚቻል መልኩ ማቅረብ ተገቢ ይሆናል።

የስነጽሁፍንና የጋዜጠኝነትን መስተጋብር ለማስረዳት የበዓሉ ግርማ ስራ በማሳያነት ቀርቧል። በ1961ዓ.ም መነን መጽሄት ላይ የሽፋን ታሪክ ሆኖ የቀረበው "የመኖሪያ ቤት ችግር" የሚለው መጣጥፍ ጥሩ ዘይቤዎችና የአወቃቀር ስልት ይታይበታል። ትክክለኛ ጽሁፋዊና ስብአዊ ማስረጃዎችን በማጣቀስ፣ የራሱንም ምልከታ በማከል የታተመ ጽሁፍ ነው። በጽሁፉ በዓሉ በዘመኑ ጎልተው ይታዩ ከነበሩ ችግሮች አንዱን አንስቷል። ይህን ችግር ሲያቀርብም አስማቀፋዊ ባህርይ ያለው መሆኑን በመጥቀስ ግርርነቱን አለሳልሶታል።

ይህ ማህበራዊ ችግር ምን ያህል ስፋት እንዳለው ለማሳየት በአዲስ አበባ ከተማ በቤት ችግር የሚሰቃዩ ሰዎችን በአሃዝ አመልክቷል። ለዚህም የስታቲስቲክስ መስሪያ ቤት ያወጣውን ወቅታዊ መረጃ ጠቅሷል። የከተማዋን የቤት ችግር ያባባሱት ምክንቶች ደግሞ ከገጠር እየፈለሰ የሚመጣው ህዝብ መብዛትና በየጊዜ እያረጁ የሚፈርሱት ቤቶች ቁጥር ማየል ናቸው። ቤት ለመስራት የሚያስችል ብድር የሚሰጡ ተቋማት እንደልብ አለመኖር፣ ያሉትም ሁለት ተቋማት የሚያስከትሉት ወለድ ከፍተኛ መሆኑ፣ ብድሩን ለማግኘት የሚስደው ጊዜ መርዘሙ ተስፋ አስቆራጭ መሆናቸው የግል ቤት እየተከራዩ የሚንከራተቱትን ነዋሪች እሮሮ አባብሶታል። በጽሁፉ ለችግሩ መፍትሄ የሚለውንም አስቀምጧል። ለዚህም ኃላፊነቱ የመንግስት መሆኑንና መንግስትም በጀት መድቦ እየሰራ መሆኑን አመላክቷል። የተጠቀመባቸው ስነጽሁፋዊ ቴክኒኮች፣ ማመሳሰል፣ ንቡር ጠቃሽ፣ ግነታዊ ቃላትን፣ እና ስእላዊ አጻጻፍ ናቸው።

ሁለተኛው ትምህርት የተሰጠው በዘሪሁን አስፋው ነው። ዘሪሁን አስፋው በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል የስነጽሁፍ ተባባሪ ፕሮፌሰር ነው። የዘሪሁን ርዕሰ ጉዳይ የአጭር ልቦለድ አጻጻፍ ቴክኒክና በአጻጻፍ ሂደቱ ደራሲዎችን

የሚገጥሟቸው ፈተናዎች ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በትምህርቱ መግቢያ ላይ ወደ ደራሲነት የሚገቡ ሰዎች ሊኖራቸው የሚገቡ ባህሪያትና ችሎታዎች ተዘርዝረው ገለጻ ተደርጎባቸዋል፡፡ ደራሲዎች በታሪክ መረጣ፣ በታሪክ አፈጣጠርና በትልም አወቃቀር ረገድ ማድረግ የሚገባቸውን ጥበባዊ ገጽታዎች እንዲሁም በታሪክና በትልም አወቃቀር የሚገጥሙ ፈተናዎች ተወስተዋል፡፡

በአተራረክ ዘዴዎች በተለይም የአጭር ልቦለድን አበይት ባህርያት፣ ነጠላ ግብን፣ ቁጥብነትንና ጥድፊያን ጠብቆ የመጻፍን አስፈላጊነትና እነዚህን ባህሪያት ለመጠበቅ ደራሲዎች በሚያደርጉት ጥረት የሚገጥሟቸውን ፈታኝ ሁኔታዎች አጥኚው አስረድቷል፡፡ በአጭር ልቦለድ ግጭት የማይቀር መሆኑን፣ በግጭት አገነባብ ረገድ በእጅጉ የሚተኮርባቸው መልኮች ምን ምን እንደሆኑ በመጥቀስ ደራሲዎች ልቦለዳዊ ግጭት በሚፈጥሩበት ጊዜ ማድረግ የሚገባቸውን ጥንቃቄ አሳይቷል፡፡

ዘሪሁን በአጭር ልቦለድ ኪነጥበብ ደራሲዎች የሚጠቀሙባቸውን የአተራረክ ዘዴዎች ምንነትና እንዴትነት፣ በአተራረክ ዘዴ ምርጫና አጠቃቀም ረገድ ደራሲዎችን የሚፈታተኑ ገጽታዎችን በማውሳት የአንድ መልካም አጭር ልቦለድ አተራረክ ምን መምሰል እንዳለበት አሳይቷል፡፡ ከነዚህ በተጨማሪ የአጭር ልቦለድ አጀማመርና አጨራረስ እንዲሁም የቋንቋ አጠቃቀም ምን መምሰል እንዳለበት በነዚህ በሁለቱ ረገድ ደራሲዎቹን የሚፈታተኑ መልኮች ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ አንስቷል፡፡

ሶስተኛው የዐውደ ጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ በግጥም አጻጻፍ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ የጥናቱ አቅራቢ ወንደወሰን አዳነ ሲሆን እሱም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል መምህርና በአሁኑ ጊዜ በክፍሉ የሚሰጠውን የፒኤችዲ ትምህርት በመከታተል ላይ ይገኛል፡፡

ወንድወሰን ያተኮረው ገጣሚዎች በሚጽፉበት ጊዜ ይበልጥ ትኩረት መስጠት ባለባቸው የተለያዩ ስነግጥማዊ ገጽታዎች ላይ ነው፡፡ የግጥምን ዋና ዋና አላባውያን በዝርዝር በማስረዳትና ምሳሌዎች ከየመጻህፍቱ በመውሰድ ተሳታፊዎቹ ስለስነግጥም ያላዩዋቸውን እንዲያዩ አድርጓል፡፡ የግጥምን አበይት ባህርያት ምትና ምጣኔን፣ እምቅነትን በመጥቀስ እነዚህን ጠብቆ ለመጻፍ ጥረት በሚደረግበት ጊዜ ገጣሚዎቹን የሚጋረጡባቸውን ፈተናዎች አሳይቷል፡፡ የተለያዩ ደራስያንን ግጥሞች በምሳሌነት በማምጣት ግጥም እንዴት እንደሚጻፍና እንዴት እንደማይጻፍ ገልጿል፡፡

ወንደወሰን በቅርብ አመታት እየታተሙ በወጡ የግጥም መጻህፍት ውስጥ የሚታዩትን ስህተቶች በመጥቀስ መረር ያለ ሂስ በመስጠት ተሳታፊዎቹ በግጥም አጻጻፍ ረገድ ያለውን

ፈተና እንዲያውቁት ትምህርት ሰጥቷል። በግጥም ከፍ ያለ ጥንቃቄ ስለሚያስፈልጋቸው፣ ስለቃላት አመራረጥና ተገቢ ስላልሆነ የማፈንገጥ ስልት እንዲሁም ስለጽሁፍ ገጽ መልኮች ሰፊ ትንታኔና ማብራሪያ በማቅረብ ገጣሚዎች ጉዳዩን ልብ እንዲሉት ጠንካራ ማሳሰቢያ አጥኚው ሰጥቷል። በአጠቃላይ በግጥም ፈጠራ ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ጉዳይ ፍሰጋ፣ የቃላት ምርጫ፣ የዘይቤ ፈጠራ፣ አሰነኛኘት፣ ሥርዓተ ጽህፈት በተሰኙ አብይ ርዕሶች በመከፋፈል ጉዳዩን በስፋት አሳይቷል።

አራተኛውና በዐውደጥናቱ ማብቂያ ላይ የቀረበው ጥናት በበአሉ ግርማ የአጻጻፍ ስልት ላይ ያተኮረ ነው። በጥናቱ አቅራቢ ዘሪሁን አስፋው በበዓሉ ግርማ ስድስት ልቦለዶች ውስጥ የሚታዩትን የአጻጻፍ ስልት የተወሰኑ መልኮች ነው ያሳየው። አጥኚው፣በዓሉ ግርማ በሁሉም ልቦለዶች አጭር ዐረፍተነገሮችን፣ በዐረፍተነገሮቹ ውስጥም የድርደራንና የድግግም ሐረጋዊና ዐረፍተነገራዊ ቅንብርን እንደሚመርጥ በምሳሌ አሳይቷል።

ከበዓሉ ግርማ ያጻጻፍ ስልት ምርጫዎች መካከል አነጻጻሪ የተባለው ዘይቤ ጎልቶ እንደሚታይና በአብዛኛው ደራሲው ይህን ዘይቤ የገጸባህሪያቱን ማንነት፣ ድርጊታቸውንና አሳባቸውን ለመግለጽ እንደሚያውለው አህዛዊ ማስረጃዎችን በማምጣት አጥኚው አሳይቷል። በዘይቤዎቹ በዓሉ ግርማ ለምስል መፍጠሪያነት አዘውትሮ የሚገለገልባቸውን ሰዋዊና ተፈጥሮአዊ ነገሮች ከልቦለዶቹ በማውጣት የምስል ምንጮቹን በአህዛዊ ስሌት ያላቸውን ቅደም ተከተል ተንትኗል። ዘሪሁን በጥናቱ ግኝት በዓሉ ግርማ በአብዛኛው በቤት ውስጥ የሚገኙ ዕቃዎችን ለምስል መፍጠሪያነት የሚመርጥ መሆኑን አሳይቶ በአጠቃላይ በዓሉ ግርማ ስልተኛ ደራሲ መሆኑን በመግለጽ ነው የደመደመው።

## 4. የዐውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች አስተያየት

በዐውደ ጥናቱ ማጠናቀቂያ ተሳታፊዎቹ ስለዐውደ ጥናቱ ያላቸውን አስተያየት ሰባት ጥያቄዎችን ይዞ በተዘጋጀው ቅጽ ላይ እንዲሰጡ ተጠይቀዋል። በዐውደ ጥናቱ ከተገኙት 50 ተሳታፊዎች መካከል 36ቱ (72%) ቅጹን ሞልተው መልሰዋል።

በአስተያየት መስጫው ቅጽ ውስጥ ከተካተቱት ጥያቄዎች መካከል አንዱ ተሳታፊዎቹ የዐውደ ጥናቱን ጠቃሚነት በደረጃ እንዲያስቀምጡ የሚጠይቅ ነው። የተሳታፊዎቹ ምላሽም እንደሚያመለክተው 33ቱ (92%) ዐውደ ጥናቱ በጣም ጠቃሚ ሆኖ ያገኙት መሆኑን ገልጸዋል፡ ፡ ሁለት ተሳታፊዎች (6%) ዐውደ ጥናቱ ጠቃሚ ነው ብለዋል። አንድ ተሳታፊ (2%) ሀሳብ ሳይሰጥ ቀርቷል።

ተሳታፊዎቹ ስለበዓሉ ግርማ ፋውንዴሽን ከዚህ ቀደም ያውቁ እንደሆነ ተጠይቀው መጠይቁን ከሞሉት ተሳታፊዎች መካከል 19ኙ (53%) ቀደም ሲል ስለበዓሉ ግርማ ፋውንዴሽን የሰሙ መሆናቸውን ሲገልጹ 17ቱ (47%) ስለፋውንዴሽኑ ቀድመው አለማወቃቸውን አመልክተዋል።

በዐውደ ጥናቱ የቀረቡት ርዕሰ ጉዳዮች የመጻፍ ተግባራቸውን በማጠናከር ረገድ እገዛ ያደርጉ እንደሆነ ተሳታፊዎቹ ተጠይቀው 31ዱ (86%) የተነሱት ርዕሰ ጉዳዮች የመጻፍ ተግባራቸውን የሚያጠናክሩላቸው መሆናቸውን ገልጸዋል።

ለተሳታፊዎች ከቀረቡት ጥያቄዎች አንዱ ከዐውደ ጥናቱ ያገኙት አዲስ ሀሳብ ምን እንደሆነ እንዲያሰፍሩ የሚጠይቅ ነው። በዚህ ረገድ ከተገኙ ምላሾች መካከል ለአብነት የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል፡-

- በጽሁፍ ውስጥ ያሉ ገለጻዎችን በአሀዛዊ ትንታኔ መግለጽ መቻሉ
- በጥበባዊ ፍንገጣና በስህተታዊ ፍንገጣ መካከል ስለአለው ልዩነት
- በጽሁፍ ውስጥ በተደጋጋሚ የሚታዩ የቃላት ግድፈቶችን ለማስተካከል መደረግ ስለአለበት ጥረት
- የግጥም ችሎታ በትምህርት መታገዝ መቻሉ
- የደራሲዎች ስለባህልና ወግ መቆርቆር
- ስለበዓሉ ግርማ ያጻጻፍ ቴክኒክ
- በአጻጻፍ ስልት መጤን ስለአለባቸው ጉዳዮች
- ስለደራሲ ባህሪያት
- ግጥም ለመጻፍ ምን ምን ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት እንዳለባቸው

የበዓሉ ግርማ ፋውንዴሽን በምን አይነት ፕሮግራም ወይም በምን ጉዳይ ላይ እንዲያተኩር ይፈልጋሉ ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ ተሳታፊዎች ከሰጧቸው ምላሾች መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ፡-

- የስኮላርሺፕ ፕሮግራም ይበልጥ ቢጠናከር
- በኢትዮጵያ ስነጽሁፍ ጥናት የሚያደርጉ ሰዎችን ማበረታታትና የጥናታቸው ውጤት የሚታተምበትን መንገድ ማመቻቸት
- በስነጽሁፍ ስራ ላይ ለተሰማሩ ሰዎች ስልጠና መስጠት
- የተለያዩ ደራስያን በአቅም ማጣት ምክንያት ያላሳተሟቸውን መጻህፍት ለማሳተም እገዛ ማድረግ

- ወጣቶች ስለ በዓሉና ቀደምት ደራስያን የሚማሩበትን መንገድ ማዘጋጀት
- መሰል ዐውደ ጥናቶችን ደጋግሞ ማቅረብ
- ደራሲ በዓሉ ግርማ በየጋዜጣው ላይ የጻፋቸውን ጽሁፎች በአንድ መድበል ታትመው እንዲቀርቡ ማድረግ
- የኢትዮጵያ ስነጽሁፍ በዓለም ደረጃ እንዲታወቅ ማድረግ
- ፋውንዴሽኑ ከዚህ ሰፋ ባለ ሁኔታ ራሱን ማሳወቅ ቢችል
- የስነጽሁፍ ውድድር ማዘጋጀት
- ወጣት ደራሲያንን መሸለም

## 5. የዐውደ ጥናቱ መዝጊያ

ዐውደ ጥናቱ አስተባባሪው ተሳታፊዎቹ ንቁ ተሳትፎ በማድረግ ዋጋ ያላቸው ጥያቄዎችን፣ አስተያየቶችንና ተጨማሪ ሀሳቦችን በመስጠት ቀኑን ሙሉ በትጋት በመዋላቸው አመሰገነ። በተጨማሪ ለዐውደ ጥናቱ መሆን ከፍ ያለ አስተዋጽኦ ያደረገችውን መስከረም በአሉን፣ የበአሉ ግርማን ቤተሰብና የፋውንዴሽኑን መስራቾች እንዲሁም ለዐውደ ጥናቱ መሳካት አስተዋጽኦ ያደረጉትን በማመስገን የዐውደ ጥናቱን ፍጻሜ አስታወቀ።

የመጨረሻውን የመዝጊያ ንግግር መስከረም በዓሉ አደረገች። በንግግሯም ለዐውደ ጥናቱ መሳካት አዘጋጆቹን፣ ለንቁ ተሳትፎና አስተያየት ተሳታፊዎቹን፣ አመስግና ተሳታፊዎቹ ከበዓሉ ግርማ ፋውንዴሽን ጋር ያላቸውን ግንኙነት እንዲያጠናክሩ ፋውንዴሽኑም ሀሳባቸውን በመቀበል የወደፊት ስራውን እንደሚያከናውን ገልጻ ለሁሉም መልካሙን ተመኝታለች።

በመጨረሻ፡ ከተሳታፊዎቹ፡ የተዘጋጀው፡ የተሳትፎ፡ ምስክር፡ ወረቀት ተሰጥቷል።